# በከሰሩ ፖለቲከኞችና አክራሪዎች ጋብቻ የሚቀፈቀፉ ሽብርተኞችና መዘዛቸው (፪)

## አብዱልአዚዝ 08/05/13

ሽብርተኝነት ህዝቦች በሠላም በነፃነትና በተረጋጋ ሁኔታ ኑሮአቸውን እንዳይመሩ አደገኛ እንቅፋት በመሆኑ የሠው ልጅ በሙሉ እጅግ በሚሠጋውና የአእምሮ እረፍት የሚነሣው በመሆኑ ለህዝቦች ሁሉ ሽብርተኝነትን መዋጋት የህልውና ጥያቄና ግዴታ ሆኗል፡፡

መንግስት ይህንኑ እየከፋ የመጣውን የሽብርተኝነት አደጋ ሥጋት መከላከል እንዲቻለው የተለያዩ ህጎችንና አዋጆችን አውጥቶ ተግባራዊ በማድረጉ የከሠሩ ፖለቲከኞችና በእስልምና ሃይማኖት ስም የሚነግዱ ጽንፈኞች "ሽብርተኛ በሌለበት የፀረ ሽብርተኝነት ህግ አያስፈልግም" ሲሉ ቢሟገቱም የፀረ ሽብርተኝነት ህጉን ያረቀቀውና ያፀደቀው መንግስት በሚገባው ደረጃ ተግባር ላይ አውሎ ባለመገኘቱ የአክራሪነት አደጋ ከከሠሩ ፖለቲከኞች አጀንዳ ጋር ተመጋግቦና ተደጋግፎ ሽብርን እየወለደ የሚገኝበት ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡

ከዚህ ቀደም በነበረው መጣጥፌ  ከነዚህ ሰዎች ጋብቻ የተወለዱቱ ሽብርተኞች አክራሪነት ለኢትዮጵያ ስጋት መሆናቸውን በተመለከተ የሰሞኑን የከሠሩ ፖለቲከኞች በሠላማዊ ሠልፍ ስም ያደረጉትን ግርግር እና የፀረ ሽብር ሕጉ ይደለዝ ጥያቄ በእስልምና ሃይማኖት ስም ከሚነግዱ ሃይሎች ጋር በማያያዝ የተሠራ ጥናት  ማረጋገጡን እና ከዚህም ውስጥ ይህ የአክራሪነት አደጋ ወደ ሽብርተኝነት ደረጃ ሲሸጋገር ከሚኖረው ጦስ ውስጥ በህይወት እና ንብረት ላይ የሚያስከትለውን አደጋ በተመለከተ ለማብራራት ሞክሬአለሁ፡፡

በዚህ የሃይማኖት አክራሪነትና የከሠሩ ፖለቲከኞችን በተመለከተው የመጨረሻ ክፍል መጣጥፌ አደጋው የሚያስከትለውን የተቀሩ ጉዳቶችን በተመለከተ ለመዳሠሥ እሞክራለሁ፡፡

የሃይማኖት ጽንፈኝነትና አክራሪነት ከከሠሩ ፖለቲከኞች ጋር ተያይዞ እያስከተለ ያለውን አደጋና ሥጋት በተመለከተ አልገባንም ሲሉ ለማሞኘት የሚሞክሩትንና በነዚሁ የከሠሩ

ፖለቲከኞች ልሣን ላይ የሚወጡ ጽሁፎችን በተመለከተ ሃሣብ በሠነዘርኩበት የመጀመሪያ ክፍል መጣጥፌ አክራሪነትና ጽንፈኝነት በሌለበት ባይደነፋና ባይነገር ይመረጣል፡፡ ማን አክራሪና አክራሪነት ምን ማለት እንደሆነ? አልገባንም ለሚሉትና መሠል ግለሠቦች የገዛ ሃሣባቸው የጽንፈኝነት ደረጃና አክራሪነት ወደ ሽብር እየሄደ መሆኑን የሚያመላክት ስለመሆኑ ነጥብ በነጥብ ጠቅሼ የገለጽኩኝ ሲሆን በዚህ መጣጥፌ ተጨባጭ ታሪኮችንና ጥናቶችን መሠረት አድርጌ ማን አክራሪና አሸባሪ እንደሆነ በዚህም የተነሣ ህዝቡ ምን ያህል ሥጋት ላይ ስለመሆኑና እንቅልፍ ማጣቱን እንደማወሳ ተነጋግረናል፡፡

ስለሆነም እንደተለመደው የከሠሩ ፖለቲከኞች እና በሃይማኖት ስም የሚነግዱ አክራሪዎች እየፈጸሙ የሚገኙት ሁከት የሽብርተኝነቱን ሥጋት ደረጃና ከፍታ እንዴት እንደሚገልጽ ተጨባጭ የሆኑ የትናንት ማሣያዎችንና ዓለም አቀፍ ሰነዶችን እያነሣሁ ትርክቱን በመቀጠል እንደመፍትሄ ምን መደረግ አለበት ስል የግሌንም አስተያየት በመደምደሚያነት እሠጣለሁኝ፡፡

የእስልምናን ሠላምነትና አስተምህሮ ጠንቅቀው የሚያውቁትና ልቅም አድርገው የሚዘረዝሩት፣ ስለሰላምና መቻቻል ተናግረው የማይደክሙትና ሠላም ሆነው ስለሠላም የሚዘምሩት ታላቁና መንፈሣዊው አባት ሼህ ኑር ይማም ከሠሞኑ "ስለሰላም ቆመናል ድምፃችን ይሠማ" በሚሉና ከጀርባ ግን ሌላ ሤራ ያነገቡ አክራሪ ሃይሎች አሠቃቂ በሆነ ሁኔታ ህይወታቸው አልፏል፡፡

የኢትዮጵያ የመጀመሪያው የአህሉሽና ወልጀምዳ ሴሚናር ሠሞኑን በኡማ ሆቴል በተደረገ ወቅት ታላላቅ የሚባሉትና የእምነቱ አባት ሊቃውንቶች “የሼ ኑር ይማም ግድያ የሃይማኖት ጽንፈኝነት ወደሽብርተኝነት መሸጋገሩን ያሳያል” ማለታቸው እና እነዚሁ ሊቃውንት አባቶች የሃይማኖት ጽንፈኞች በሼክኑር ይማም ላይ የፈጸሙት አሠቃቂ ግድያ ጽንፈኝነትና አክራሪነት የእስልምና ሃይማኖትን እንደማይወክል ማሣያ መሆኑን ጠቅሠው ጽንፈኞችና አንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲዎች የእስልምና ሃይማኖትን የሥልጣን መወጣጫ አድርገው መጠቀም እንደሌለባቸውና የፖለቲካ ፓርቲዎቹ ሃይማኖቱን እንደ ሽፋን መጠቀምን አቁመው በፖለቲካው መድረክ እንዲወዳደሩ ማሳሰባቸው የከሠሩ ፖለቲከኞችና በሃይማኖት ስም የሚንቀሳቀሱ ጽንፈኞች በፈፀሙት ጋብቻ ከአክረሪነት ወደሽብርተኝነት መሸጋገራቸውን ለሚያመላክተው ትረርክቱ እውነትነት ተጨባጭ ማረጋገጫዬ ነው፡፡

ከእለት እለት እየረቀቀ የመጣ ሽብርተኝነት፣ የወቅቱ የዓለማችን አሳሳቢና ከፍኛ ሥጋት እየሆነ በመምጣቱ በርካታ አገራት ለጉዳዩ ልዩ ትኩረት በሀመሥጠት ላይ ናቸው፡፡

የኛውን ለየት የሚያደርገው ደግሞ በሃይማኖት ሽፋን የሚደረግና ከከሡሩ ፖለቲከኞች ጋር ተመጋግቦ በውጭ ሀይሎች እጅ የሚሾር መሆኑ ነው፡፡ ይህ ተጨባጭ ሃቅ በለበት ሁኔታና በተግባር እየተገለፀ ባለበት ሠዓት ላይ መንግስት ያወጣውን ህግ በተግባርና በማያዳግም መልክ መጠቀም ሲገባው ነጋ ጠባ ወደምክርና ተግሳፅ ማዘንበሉ ሥጋታችንን የከፋ ያደርገዋል፡፡

እነዚህ አክራሪዎችና የከሡሩ ፖለቲከኞች ሽብርተኝነት በሌለበት የፀረ ሽብር ህግ አያስፈልገንም ቢሉምና ቆርጠው ቢቀጥሉም፣ በየትም ሃገር የሌለና ሥራ ላይ ያልዋለ ህግ ነው ብለው ቢያደነቁሩንም የተለያዩ ሃገራት የሽብርተኝነትን አሥከፊነት፣ አደጋና የአፈፃፀሙን ውስብስብነት ግምት ውስጥ በማስገባት ራሡን የቻለ የወንጀለኛ መቅጫ ህግና ወንጀሉን የማጣራት ሂደት ሥርዓት አውጥተው እየሡሩበት ይገኛሉ፡፡ እንግሊዝ፣ አሜሪካ፣ ካናዳ፣ አውስትራሊያ፣ ህንድ፣ ደቡብ አፍሪካ  እና ዩጋንዳ ሊጠቀሡ የሚችሉና ከመሆናቸውም በላይ እነዚህ ሃገራት ከእኛ በራቀ ደረጃ የበለጸጉ መሆናቸው እና እኛ ደግሞ ከድህነት ጋር የተያያዝነውን ትንቅንቅ በማደናቀፍ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ በመሆን ጠሡ የት ድረስ የሚረዝም ችግር እንደሚያመጣ በመገንዘብ አዋጁን ማውጣቱ ብቻ ሳይሆን በተግባር ላይ  ማዋል አሥፈላጊ መሆኑን ያመለክታል፡፡

እነዚህ የከሡሩ ፖለቲከኞችና የሃይማኖት ጽንፈኞች ተደጋግፈውና ተመጋግበው በውጭ ሃይሎች በመነዳት የመፈጸሙት ተግባር አክራሪነትን ተሻግሮ ወደሽብር በማደጉ ካስከተለው የሠውና የንብረት አደጋ ባሻገር ያሉትን አደጋዎች እስኪ ደግሞ እንመልከታቸው፡፡

ግጭት በማንኛውም ምክንያት ሲፈጥር ለልማት ስራ እንቅፋ መሆኑ አይቀርም፡፡ በአገራችን የተፋጠነ ልማት ለማምጣት በሚካሄደው ጥረት ትክክለኛ ፖሊሲና ስትራቴጂ መያዛችን ለድል አንዱ ወሳኝ ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡ ነገር ግን ልማትን እውን የማድረግና በዚህም ህዝቡን የመጥቀም ጉዳይ ትክክለኛ ፖሊሲና ስትራቴጂ ከመንደፍ ባሻገር ይህንኑ በጥብቅ ተግባራዊ የማድረግ ጉዳይ ጭምር ነው፡፡ ሁሉም የልማት ተዋናዮች በተቀየሰው ፖሊሲና ስትራተጂ መሰረት በነፃነት ተንቀሳቅሰው ገንዘባቸውን፣ ጉልበታቸውንና

እውቀታቸውን በመጠቀም ማልማት ሲችሉ የተፋጠነና ህዝብ የሚጠቀምበት ልማት እውን ይሆናል፡፡ ኢንቬስተሩ በሰላም እጦት ሳይታወክ ከቦታ ቦታ በነፃነት ተንቀሳቅሶ መስራት መቻል አለበት፡፡ ሰራተኛውም በሰላም ወጥቶ ገብቶ በምርታማ ተግባር ውስጥ በመሰማራት አዲስ ሃብት መፍጥር መቻል ይገባዋል፡፡ ሰላም በተለይም ዘላቂና አስተማማኝ ሰላም ሲኖር ካፒልና ጉልበት በሰላም ተንቀሳቅሰው አዲስ ሃብት ለመፍጠርና የአገርን እድገት ለማረጋገጥ ይችላሉ፡፡ ከዚህ በተለየ አኳኋን ሰላም በሰበብ አስባቡ ከጠፋ የካፒታልም ሆነ የጉልበት ነፃና ሰፊ እንቅስቃሴ ይገደባል፡፡ ሰው ሰርቶ ስለመበልፀግ ወይም መኖር ሳይሆን ራሱን ከአደጋ ስለመጠበቅ እያወጣ እያወረደ ሳይንቀሳቀስ ይቀራል፡፡ ጉልበታችንና ካፒታላችን በሰላም እጦት ይመክናል፡፡

በሃይማኖት ሽፋን የሚቀሰቀስ ግጭትም በልማታችን ላይ ቀጥተኛና አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳርፋል፡፡ ወይም ደግሞ ትልልቅና በአንዴ ብልጭ ብሎ ድርግም የሚል ወይም ቀጣይነት ያለው ሊሆን ይችላል፡፡ መጠኑም ሆነ ተከታታይነቱ ምንም ይሁን ምን  ይህ የሰላም መታወክ ልማትን ክፉኛ የሚጎዳ መሆኑ አይቀርም፡፡ ግጭት ምንጊዜም ቢሆን በህብረተሰብ ላይ አሉታዊ ስነልቦናዊ ተፅእኖ የሚያሳርፍ መሆኑ ብቻ በልማት ላይ ገዳቢ ሚና ይጫወታል፡፡ በሃይማኖት ሽፋን በሚቀሰቀስ ግጭጥም ባለሃብቱ ገንዘቤን ካፈሰስኩ በኋላ ግጭቱ ተባብሶ ለመስራት የማልችልበት ሁኔታ ቢፈጠርስ ብሎ ማሰቡ አይቀርም፡፡ ሰራተኛውም ከቤቱ ወደስራ ወይም ከስራ ወደቤቱ ሲመላለስ ለአደጋ እንዳይጋለጥ በመፍራት ከምርት ተግባራቱ  ይስተጓጎላል።

 በሃይማኖት ሽፋን የሚቀሰቀስ ግጭት ሰላምና መረጋጋትን በማደፍረስ የልማት ግስጋሴን ከሚያደናቅፈው ባልተናነሰ ሁኔታ በሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ማሳረፉ አይቀርም፡፡ ግጭት የልዩነት መፍቻ መንገድ ሲሆን ከህጋዊና ሰላማዊ መንገድ ይልቅ የሃይል መፍትሄ ቅድሚያ ማግኘቱን ያመለክታል፡፡ የሃይል መፍትሄ በጥቅም ላይ ሲውል ደግሞ ጉልበተኛው በአቅመ ደካማው ላይ መግነኑ አይቀርም፡፡ አቅመ ደካሞች የህግ ከለላ አጥተው በጉልበተኞች  ምህረት ስር ይወድቃሉ፡፡ ጉልበት የተሰማቸው ወገኖች የእያንዳንዱን ዜጋ መብት የሚፈቅዱና የሚከለክሉ እስከመሆን ይደርሳሉ እየደረሱም ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ሰብዓዊ መብቶች ለአደጋ መጋለጣቸው አይቀርም፡፡

ግጭት የሃይል መፍቻ መንገድ ሲሆን ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ፣ የመከራከርና ምክንያታዊ በሆነ ሙግት የመሸናነፍ እድል ይጠባል፡፡ ወይ ከነአካቴው ይጠፋል፡፡ ጉልበት የሃይል መፍቻ መንገድ ሲሆን የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን መብትና ጥቅሞች በድርድርና በመቻቻል ሚዛናዊ በሆነ አኳኋን የማስጠበቅ እድል ይጠባል ወይም ጨርሶ ይዘጋል፡፡ ስለዚህም ዴሞክራሲ ብቻ ሳይሆን መልካም አስተዳደርም አብሮ ይጠፋል፡፡ ጉልበት የልዩነት መፍቻ በሆነበት በየትኛውም አካባቢ ዴሞክራሲ ለአደጋ መጋለጡ አይቀርም፡፡ በቀበሌም ይሁን በወረዳ፣ በክልልም ይን በአገር ደረጃ የጉልበት መፍትሄ የልዩነት ማስወገጃ ሲሆን የሚከተለው ውጤት የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መጥፋት ወይም መረገጥ መሆኑ አይቀርም፡፡ በመሆኑም ለሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር ስንል ሃይማኖትን በሽፋንነት የሚጠቀሙ የከሰሩ የአገር ውስጥና የውጭ ሃይሎች የሚቀሰቅሱትን ግጭት በምሬት መታገል ይገባናል፡፡

አገራችን ካለፉት 22 ዓመታት ወዲህ በሰላም፣ በልማትና ዴሞክራሲ ጎዳና እየተራመደች ትገኛለች፡፡ በዚህ ሂደት መልካም ነገር ፈፅሞ የማይዋጥላቸው ተቃዋሚዎች ሳይቀር ሊክዱት በማይችሉት ደረጃ አገራችን በሁሉም መስኮች በመለወጥ ላይ ነች፡፡ይህ ባለበት አግባብ

ሃይማኖትን ሽፋን ላደረገ ግጭት እና በከሰሩ ፖለቲከኞችና አክራሪያን ጋብቻ ላይ ከደነስን ስለአገራችን ተይዞ ባደረው አሉታዊ ግንዛቤ ላይ መደመሩ አይቀርም፡¨አገራችን ከራሷ አልፋ ለአፍሪካ ሰላም ከፍተኛ አስተዋፅኦ የምታበረክት አስተማማኝ የሰላም አገር መሆኗ ተደፍቆ በረባ ባልረባው ምክንያት በሚቀሰቀስ ግጭት ጥላሸት መቀባቷ አይቀርም፡፡ ይህም ተመልሶ ኢንቨስትመንትን የመሳብ እድላችንን ማጥበቡ፣ የቱሪስት ፍሰትን መቀነሱ

ከፍ ሲል ከተጠቀሱት ከነዚህ ጉዳቶች በመነሳት የከሰሩ የአገር ውስጥ ፖለቲከኞችም ሆነ የየራሳቸው አጀንዳ ያላቸው የውጭ ሃይሎች በሃይማኖት ሽፋን ግጭት ለመቀስቀስ የሚያደርጉትን ጥረት በቸልታ መመልከት ምን ያህል ሊጎዳን እንደሚችል ለመገንዘብ አያዳግትም፡፡ ሃይማኖትን ሽፋን ያደረገ የፖለቲካ ግጭት ራሱን የሃይማኖትን እኩልነት ጨምሮ ሁሉንም ድሎች የመቀልበስ ወይም በከፍተኛ ደረጃ የመሸራረፍ አደጋ ማስከተሉ ኤቀርም።

በአጠቃላይ በዚህና ከዚህ ጋር ተያያዥ በሆኑት የቀደሙ መጣጥፎች ላይ እንደተገለፀው ኢትዮጵያ የሽብርተኝነት ሥጋትና አደጋ በከፍተኛ ደረጃ ባንዣበበት የአፍሪካ ቀንድ የምትገኝ ከመሆኗም በላይ በስተሠሜን በኩል የኤርትራው የኢሣያስ ቡድን የእናት ጡት ነካሽ ከሆነው ግንቦት 7 ጋ አብሮ የአገራችንን ሠላም ፀጥታና የልማት እንቅስቃሴ ለማናጋት (የግንቦት 7ቱ የአሸባሪ ቡድን መሪ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ከሠሞኑ ከኢሣያስ መንግስት የተቀበለውን 500 ሺህ ዩሮ ያስታውሷል) ሆን ብሎ የትርምሥ ስትራቴጂ በመንደፍ አንዳንዶቹን አስርጎ በማስገባት እንደዚሁም በአገር ውስጥ ያሉ ፀረ ሠላም ሃይሎችን እና የከሠሩ ፖለቲከኞችን በማደራጀት በማሠልጠን በማስታጠቅና በማሠማራት፣ በአናቱም በሽብር ሚዲያዎቻቸው የሃይማኖት ጽንፈኞችን አጀንዳ በማራገብና አክራሪነትን በማበረታታት በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች በሠላማዊ ህዝብና በንብረት ላይ የሽብር ተግባር የመፈፀም ሙከራ አድርገዋል፤ በማድረግም ላይ ይገኛሉ፡፡ ይሄም በመሆኑ ከፀረ ሠላም አሸባሪ ቡድኖች የሚሠነዘሩ የሽብር ጥቃቶችን በበቂ ሁኔታ ለመመከት በላያችን ላይ ያንዣበበውን ሥጋት በመቅረፍ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ተቋማት በህግ ማጠናከር እጅግ ወሣኝና ቁልፍ ጉዳይ ሲሆን ተቋማቱን በህግ ከማጠናከሩ በተጨማሪ የሽብርተኝነት ጥቃቱን አስከፊነትና ልዩ ባህሪይ ግምት ውስጥ በማስገባት አደጋውን ለመከላከል የሚያሥችል ራሡን የቻለና ህገመንግስቱን መሠረት ያደረገ እንዲሁም 12ቱን ዓለም አቀፍ (Anti terrorism Conventions) የፀረ ሽብር ስምምነቶች መሠረት በማድረግ የወጣውን የፀረ ሽብር ህግ ከማስተማር በዘለለ ትርጉም ወዳለው ሥራ ማስገባትና መፈጸም ጊዜው የሚጠይቀው ጉዳይ በመሆኑ እፎይ ብለን የእለት እንጀራችንን እንድንጋግርና ከድህነት ጋር የተያያዝነውን ፍልሚያ በድል እንድናጠናቅቅ ከመንግሥት ብዙ ነገር እንጠብቃለን፡፡ በዚህና አስከፊ በሆነው ድርጊት ውስጥ አውቀው በድፍረት ሣያውቁ በስህተት እጃቸውን ለነከሩት ሁሉ ልቦና እንዲሠጣቸውም በዚህ አጋጣሚ ምኞቴን በመግለጽ ላበቃ ስልና ሐሙስ ምሽት የዚህን ጹሁፍ የመጨረሻ አርትኦት በመስራት ላይ ሳለሁ ምናልባት አንዳች የተለወጠና የተለየ ነገር ካለ በሚል የከሰሩ ፖለቲከኞች እና የኢክራርያኑ የመፈራረሚያ የውል ሠነድ ወደሆነው "ድምፃችን ይሰማ "ማህበራዊ ድረ ገፅ አማተርኩ፡፡በአርብና የመጨረሻው የረመዳን ጁምአ ሁሉ ሙሉ ሁሉ ዝግጁ መሆኑን የሚያረጋግጥ መልዕክት ተመለከትኩ፡፡ ስለሆነም አርብን መጠበቅ ለዚህ ፅሁፍ አስረጂ የሆኑ ዋቢዎችና የመፍተሔ አማራጮች አስፈላጊ ሆኖ አገኘሁትና ወደ አንባቢያን መድረክ ከመላክ ተቆጠብኩ፤ በአናቱም የፌደራል ፖሊስ የሠጠው መግለጫ ሁሉ ሙሉን የሁሉ ዝግጁን መልዕክት

የእኔን ብቻ ሳይሆን የብዙዎቹን ቀልብ የሳበ ሆነ፡፡ በእርግጥ በትርክቱ በተደጋጋሚ እንደገለፅኩት አጀንዳው የሃይማኖት ሳይሆን በአክራሪያኑና በከሰሩ ፖለቲከኞች ጋ ብቻ በሚቀፈቀፉ ሽበርተኞች ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል መናድ ነበርና በዚህ አብዛኛው ሙስሊም ተሣታፊ ሊሆን እንደማይችል በመገንዘብ እነዚህ ሃይሎች ላልተወሰነ ጊዜ አብዮቱን ሠርዘናል፡፡ሲሉ ድምፃችን ይሰማ በሚለው መድረካቸው ገለጹ፡፡ ይህ ውሳኔ በሁለት ምክንያት እሰየው የሚያስብል ሆኖ አግቼዋለሁ፡፡ አንደኛው ሰርተን እንዴት እንመለሳለን ብለን ለሰጋነው ቢያንስ እፎይታ የመስጠቱ ጉዳይ ሲሆን ሁለተኛው ምናልባት እነዚህ ሃይሎች ወደቀልባቸው የሚመለሱበት የመጀመርያ አጋጣሚ አጋጣሚ በመፈጠሩ፡፡

የሆኖ ሆኖ ግን እነዚህ በተለይ በዚህ ተግባራቸው ኪሳቸውን ሞልተው የተረፈና ጥይት የተቀባበሉት ሃይሎች ምሽቱን በአሜሪካው ሬዲዮ ማታ ቢፎክሩም ቅዳሜን የምንሰማው ይኖራል በማለት አሁንም መጣጥፌን ለንባብ ከማብቃት ታቅቤ የቅዳሜን ጋዜጦች ጠበኩ፡፡ የመጀመርያም የመጨረሻም ትኩረቴ የጠረጠርኩትና የድምፃችን ይሰማ ድረ ገጽ ሌላኛው ገጽታ የሆነው ፋክት መጽሄት ላይ ነበርና ጥርጣሬዬም ትክክል እንደነበር የሚያረጋግጥ መረጃ የከሠሩ ፖለቲከኞችና አክራርያን ጋብቻ ቅፍቅፍ አንዱ የሆነውና በጋዜጠኛ ቆብ የሚንቀሳቀሰው ተመስገን ደሳለኝ ለህገ መንግስታዊ ሥርአቱ አድረናል በሚሉ ግለሰቦች የወላጆቻችን ጋብቻ አይፈርስም የሚልና ይልቁንም ይህን ለህገ መንግስታዊ ሥርዓቱ ዘብ ቆሜለሁ የሚለውን ሃይል እድሜ ካላሳጠርን የወላጆቻችን ትዳር እንደሚፈርስና እኛም እንበተናለን ሲል ለወንድም እህቶች መልእክቱን አስተላልፎ አገኘሁት፡፡

በተለይ ተመሥገን የግፉአን ዕድሜ ስንት ነው? በሚል ለዘረዘራቸው አመጽ ቀስቃሽ ትርክቶቹ በሌላ መጣጥፍ የምመለስበት ሆኖ አሁንም ግን ከእነዚህ የከሥሩ ፖለቲከኞችና አክራሪያን የተቀፈቀፉ ሽብርተኞች እንዳፈገፈጉ እንጂ እንዳልሞቱ የሚያረጋግጠውን ተከታይ የተመስገንን ትርክት ጉዳዩ የሚመለከተው አካል አጥብቆ እንዲያይልን እና እንዲፈትሽልን ተማጽኖአችንን አሁንም በድጋሚ አቀርባለሁ፡፡

"ህጉ የኢ-ፍትሃዊነት ባሪያ የሚያደርግህ ከሆነ ህጉን አታክብር/ጣሠው እንዲል ታዋቂው የህዝባዊ እምቢተኝነት መምህርት ሔነሪ ዴቪድ ቶሮ ራሡ ህጉን መገዳደሩ ፍትሃዊ አካሄድ ነው፡፡" በማለት ወላጆቻቸው የሆኑት የከሥሩ ፖለቲከኞችና አክራሪያን እንኳንሥ

እስረኛ ይለቀቅ ለማሉት ቀርቶ የሥርዓት ለውጥ ለማምጣትም ፈቃድ መጠየቅ እንደሌለባቸው አሣሥቧል፡፡ ቀጥሎም የግፉአንን የመከራ ፍፃሜ ለማወጅ የማንም ፈቃድ አያሥፈልግህም የምልህ ከዚህ ባለፈ በየወሩ በጭብጨባ የሚፀድቅ ህግ የለውጥ ጉዞህን እንዲያስተጓጉል መተባበር ግዴታህ አይደለም፡፡ በማለት የህዝብ  ውክልና የተሰጠውን እና ትልቁ የሥልጣን አካል የሆነውን መ/ቤት በማንቋሸሽ እናም እልሃለሁ ከድንዛዜህ ንቃ ስለፍትህ እንጂ ስለህግ አትጨነቅ---------ከመንግስትና (ለተመስገንን ፀረ አክራሪያን ተብለው ከሚታሠቡ ዜጎች) ከደጀ ሠላማቸው አትካፈል ፤ከሠንበቴአቸው አትጠጣ" የሚለው መልዕክቱ በደንብ ከማህበረ ፖለቲካ ህግጋቶች አንፃር እንዲታይልንና እንዲፈተሸልን የምንሻው ከከሠሩ ፖለቲከኞችና ከአክራሪያኑ ጋብቻ የተቀፈቀፉ ሽብርተኞች ያተረፍነውና ከላይ የተዘረዘረው መዘዝ የበለጠ ስላለመቀጠሉ ዋስትና ስለምናጣ ነው፡፡